ትምህርት 3 ቤተ ክርስቲያን

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ምንድናት?

በተለምዶ ቤተ ክርስቲያን ማለት በጥሬ ቃሉ የክርስቲያን ቤትን ወይም የጸሎት ቤትን ወይም የክርስቲያኖች መሰብሰቢያን ሊያመለክት ይችላል። መንፈሳዊ አተረጓጎሙ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። ቤተ ክርስቲያን የተባለው የአዲስ ኪዳን ቃል “ኤክሌሲያ” የሚለው ሲሆን በሰፊው ትርጉሙ ማናቸውም ጉባዔ ማለት ነው (ሐዋ.7፡38፤ 19፡32፤41)። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎሙ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ማለት የአማኞች ጉባዔ ወይም ኅብረት ማለት ነው (1ቆሮ.1፡2፤ ገላ.1፡13)። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ማለት ህንጻው ሳይሆን አማኞቹ ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ እግዚአብሔርን በሁሉ አቅጣጫ ማክበር ነው (ኤፌ.1፡6፤12፤14)። ተግባሮቿ ደግሞ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

1. ወንጌልን ለዓለም ማዳረስንና አማኞችን ማጥመቅን ማስተማርንና ደቀ መዛሙርት ማድረግን - ማቴ.28፡19-20
2. አማኞችን መገንባትንና ማነጽ/ማሳደግን - ኤፌ.4፡11-16
3. ለአማኞች የአገልግሎት መስክ መሆንን - 1ቆሮ.12
4. አማኞች ጥፋትን ሲያጠፉ መገሰጽንና መቅጣትን - ማቴ.18፡17፤ 1ቆሮ.5፡1-13፤ 2ተሰ.3፡14-15
5. ለአማኞች የኅብረትን መስክ መፍጠርን - ሐዋ.2፡42
6. የራሷ የሆኑትን በችግራቸው መርዳትን - 2ቆሮ.8፡9፤ ያዕ.1፡27
7. መልካም የሆነውን ሁሉ ማድረግን - ገላ.6፡10

ዳግም በተወለዱና መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በኖረ አማኞች የተሰራችው ይህች ቤተ ክርስቲያን የምትባለው አካል የተወለደችው ወይም የተመሰረተችው በበዓለ ኀምሳ ቀን ነው (ሐዋ.2፡1-4፤37-42)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ምዕመን አገልግሎት ያላቸው ቢሆኑም በተለይ በመምራት አገልግሎት የተሰማሩት ሹሞች ከኃላፊነታቸው ጋር ተጽፈዋል። ከእነዚህ ሁለቱ ዋና ዋናዎቹ ኤጲስ ቆጶሳትና (1ጢሞ.3፡1-7) እና ዲያቆናት (1ጢሞ.3፡8-12) ናቸው። እነዚህ ሰዎች ምን መምሰል እንደሚገባቸውም ከላይ ያሉት ጥቅሶች ያወሳሉ።

ጥያቄዎች፡

1. የቤተ ክርስቲያንን ተለምዷዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም ስጥ ______________________________

2. የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ ምንድን ነው?______________________________

3. ከቤተ ክርስቲያን ተግባራት መካከል ጥቂቱን ጻፍ።______________________________

4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተሰጡት ሹመቶች የጎሉት የትኞቹ ናቸው?______________________________

ለ. ቤተ ክርስቲያን የምትመሰልባቸው ምሳሌዎች

ቤተ ክርስቲያን ምንና ማን መሆንዋን የበለጠ እንድንረዳ በተለይም ከክርስቶስ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማብራራት መጽሐፍ ቅዱስ ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ይገልጣታል። እነዚህ መግለጫዎች ዋና አላማቸው የቤተ ክርስቲያንንና የክርስቶስን ግንኙነት ለማሳየት ነው። እነዚህም ግንኙነቶች የተገለጡባቸው ስድስት ዋና ዋና መግለጫዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. *ራስና አካል* - (ሮሜ.12፡4-5፤1ቆሮ.12፡12-13፤ኤፌ.4፡4፤ኤፌ.5፡30፤ቆላ.1፡18) - ከዚህ አሳብ እንደምንረዳው ክርስቶስ ራስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካል ናት። እንደመሆኗም መጠን ራስ የሆነውን ክርስቶስን መታዘዝ፣በደስታ ማገልገልና መተባበር ይገባታል። አማኞች በአካል መመሰላቸው እያንዳንዱ አማኝ ብልት መሆኑን የሚያመለክት ነው። እያንዳንዱ ብልት ልዩ ልዩ ቢሆንም ማንም ከማንም አይሻልም። አንዱ ደግሞ ከሌላው መለየት የለበትም።



2. *ሙሽራና ሙሽሪት* - (2ቆሮ.11፡2፤ኤፌ.5፡25-32፤ራዕ.21፡9) - ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው ሙሽራው ወይም ባል የሆነው ክርስቶስ ሲሆን ሙሽሪት ወይም በሚስት የተመሰለችው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ያለ ገደብ እንዳፈቀረ እንረዳለን። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ለዚህ ፍቅር ምላሽ ለመስጠት ንጹህ መሆንና መታዘዝ እንደሚገባት መረዳት እንችላለን።

3. *ግንድና ቅርንጫፍ* - (ዮሐ.15፡1-5) - ከዚህ ግሩም ምንባብ እንደምንረዳው ክርስቶስ ተሸካሚው ግንድ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ወይም አማኞች ደግሞ ቅርንጫፍ ናቸው። ቅርንጫፍ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይጠበቅበታል፡-
   - በግንዱ መኖር
   - ፍሬ ማፍራት፣ ብዙ ፍሬ ማፍራት፣ የግንዱን ባህርይ የያዘ ፍሬ ማፍራት (ኢሳ.5፡1-7)፣ የወይን ቅርንጫፍ ከፍሬ በቀር ሌላ ምንም ጥቅም አይሰጥም፤ ቤት አይሰራበትም፤ የቤትም እቃዎች አይታነጹበትም (ህዝ.15፡2)።
   - ለመገረዝና ለመጥራት እሺ ማለትና መስማማት

4. *እረኛና መንጋ* - (ዮሃ.10፡11፤ ዕብ.13፡20፤ 1ጴጥ.5፡20፤ መዝ.23) - ክርስቶስ ለነፍሱ ሳይሳሳ በሞት ያዳናት የቤተ ክርስቲያን እረኛ ነው። ቤተ ክርስቲያንም የእረኛዋን ድምጽ መስማትና እርሱን መከተል ይጠበቅባታል።

5. *ሊቀ ካህናትና የካህናት መንግስት* - (1ጴጥ.2፡9፤ራዕ.1፡6፤5፡10፤20፡6) - አማኞች እንደ ካህንነታቸው ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ለሌሎቹ የመማለድና መስዋዕት የማቅረብ ዕድል አላቸው። መስዋዕቶቹም የሚከተሉት ናቸው:-

- ሰውነታቸው - ሮሜ.12፡1
- ገንዘባቸው - ለሌሎች ማካፈላቸው - ፍል.4፡18፤ዕብ.13፡16
- ምስጋናቸው - 1ጴጥ.2፡5፤ዕብ.13፡15
- መልካም ስራቸው - ዕብ.13፡16

6. *የማዕዘን ራስ ድንጋይና ሕያዋን ድንጋዮች* - (ኤፌ.2፡19-22፤1ቆሮ.3፡10-11፤ 1ጴጥ.2፡4-5) - ክርስቶስ የህንጻው መሠረትና የማዕዘኑ ድንጋይ ነው፤ሕንጻው ደግሞ የተሰራው በአማኞች ሁሉ ነው። እያንዳንዱ አማኝ እንደ ድንጋይ ይመሰላል። እያንዳንዱ ድንጋ ደግሞ ለህንጻው አስፈላጊ እንደመሆኑ እያንዳንዱም አማኝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ ነው።



ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በቀር በሌላ በማንም በምንም ላይ መመስረት አይገባትም። የማዕዘን ራስ ማለት የህንጻ የርዝመት፣ የወርድና የከፍታ አቅጣጫዎች የሚመሰረቱበት ዋና ድንጋይ ማለት ነው።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን የምትመሰልባቸው እነዚህ ምሳሌዎች የአማኝንና የምዕመንን ግንኙነት የሚያመለክቱ አመልካቾች ጭምር ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ምሳሌዎች የክርስቶስን ማንነትና የአማኝን መብትና ኃላፊነቶችም ያሳያሉ።

ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች የተጠቀሱበት ዓላማ ምንድነው?______________________________

____

____

____

2. የቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ ግንኙነቶች የተመሰሉበት ስድስት ምሳሌዎች እነማን ናቸው?

ሀ.____________________ መ.____________________

ለ.____________________ ሠ.____________________

ሐ.____________________ ረ.____________________

3. የራስና አካል ግንኙነት ምንን ያመለክታል?__________________________________

____

____

____

____

____

4. ቤተ ክርስቲያን በሙሽሪት በመመሰሏ ምን ትረዳለህ?______________________________

____

____

____

____

5. ቅርንጫፍ የሚጠበቅበት ኃላፊነቶች ምን ምን ናቸው?______________________________

____

____

____

____

____

6. አማኞች እንደ ካህን ማቅረብ የሚጠበቅባቸው መስዋዕቶች ምን ምን ናቸው?____________________

7. መሠረትና የማዕዘን ድንጋይ ለህንጻ ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆኑና ይህ ደግሞ ለክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ጻፍ።____________________

8. አንተስ የቤተ ክርስቲያን ክፍል ነህ? በመሆንህስ ምን ይሰማሃል?____________________

ሐ. ሁሉ አቀፍና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን



ቤተ ክርስቲያን የአማኞች ስብስብ እንደሆነች ተመልክተናል። ይህች የአማኞች ስብስብ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ሁለት አይነት መልክ አላት፤ እነዚህ ሁለት መልኮች ሁሉ አቀፍ ቤተ ክርስቲያንን ማለት ክርስቶስን አምነው የተቀበሉት ከዚህ በፊት ኖረው የሞቱት፤ አሁን በህይወት ያሉትና ወደፊትም የሚኖሩት አማኞች በሙሉ የሚጠቃለሉበት ስብስብ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከተወለደችበት ከጴንጤቆስጤ ዕለት አንስቶ እስከ መጨረሻው አማኝ ድረስ ያሉት በሙሉ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይጠቀለላሉ። ሁሉ አቋፏ ቤተ ክርቲያን ሁሉን ዳግም የተወለዱ አማኞች ታቅፋለች (1ቆሮ.15፡9፤ገላ.1፡13፤ኤፌ.5፡25-32)።

አጥቢያ ቤተ ክርቲያን በአንድ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚገኙ ክርስቲያኖች አንድ እምነት ስላላቸው በአንድነት ጌታን ለማምለክ፣ ቃሉን ለመማር፣ እርስ በርስም ለመተናነጽ ወንጌልን ለማዳረስና የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ሁሉ ለመፈጸም በአካባቢያቸው የተደራጁ ምዕመናን ስብስብ ናት።

አጥቢያ ማለት አካባቢ፣ ቀበሌ፣ ክልል እንደማለት ነው። እነዚህ ምዕመናን በህንጻ ውስጥ አመለኩ ወይም በቤት አጥቢያ፤ አጥቢያ ተብለው ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ፡- ኢየሩሳሌም፣ ፍልጵስዩስ፣ ተሰሎንቄ፣ ኤፌሶን፣ በሮም በአቂላና ጵርስቅላ ቤት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው።

ዛሬም በዘመናችንና በአካባቢያችን የሚገኙ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ልንጠራ እንችላለን። የጽዮን ክብር ቤተ ክርስቲያን በቫንኩቨር ቤተ ክርስቲያን፤ የመሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን፣ የተቀባ የእግዚአብሔር ቃል ቤተ ክርስቲያን፣ በሞንትሪያን የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን፣በለንደን ኦንታሪዮ የእምነት ወንጌል ቤተ ክርስቲያንና በሲያትል የሮሆቦት ቤተ ክርስቲያን ወዘተ. እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።

አንድ ህጻን ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ ከቤተሰቡ እንደሚደባለቅ አንድ አማኝ ዳግም ከተወለደ በኋላ ወዲያውኑ ከሁሉ አቀፏ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተደባልቋል። ከዚህ በኋላም ቶሎ ብሎ በአጥቢያው የምትገኝ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አለበት። ምክንያቱም ሁሉ አቀፏ ቤተ ክርስቲያን በአካላዊ መልክ የምትገለጠው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ለማዳረስ የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶችን ማለትም የጌታን ራትና የውኃ ጥምቀትን ለመፈጸም፣ ህብረት ለማድረግና እርስ በርስ ለመተናነጽ ዓይነተኛዋና ብቸኛዋ መስክ ናት። አንድ ሰው ድነትን ሲቀበል ፍጹም ሆነ ማለት ስላይደለ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባላት ፍጹማን አይደሉም። እንዲያውም ምናልባት የዳኑ የሚመስሉ ግን ያልዳኑ ሰዎች ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት በስህተት ሊገቡ ይችሉ ይሆናል።

እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎችና አገልጋዮች አሉ። እነዚህ ሁሉ የሚገለጡትና ገንቢነታቸው በተግባር የሚታየው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። በመጀመሪያ ጌታ የሾማቸው ሐዋርያትን ነበር። ሐዋርያ ማለት የተላከ ወይም መልዕክተኛ ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ሃዋርያት ጌታ ራሱ የሾማቸው ከርሱ ጋር የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ። ቀጥሎ ዲያቆናት የቤተ ክርስቲያን ማህበራዊ መሪዎች (የሃዋርያት ረዳት) ሆነው ሲያገለግሉ እናነብባለን።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ መሪዎች በተለያዩ መጠሪያዎች ተጠቅሰዋል፡-

- ኤጲስቆጶስ - 1ጢሞ.3፡1-2፤ቲቶ.1፡7
- ጳጳስ - ሐዋ.20፡28
- መጋቢ - ቲቶ.1፡7
- እረኛ - 1ጴጥ.5፡1-4

እነዚህ ሰዎች ኃላፊነታቸው ምዕመናንን መጠበቅ፣መልካም ምሳሌ መሆን፣ማስተማር፣መምከር፣መገሰጽ፣መንብኘት ወዘተ...ነው። ከመሪዎች አገልግሎት ጋር በመተባበር ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ዲያቆናት የሚባሉ አገልጋዮች ደግሞ አሉ (ሐዋ.6፡1-6)። የዲያቆናት ተግባር የመሪዎችን አገልግሎት መርዳት ወይንም ማገዝ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት፣ነቢያት፣ወንጌል ሰባኪዎች፣መጋቢዎችና አስተማሪዎች ተደርገው የተሰጡ ሰዎች አሉ (ኤፌ.4፡11)።

ከዚህም ሁሉ ባሻገር ምዕመናን ሁሉ የጸጋ ስጦታ የተሰጣቸው የአካሉ ብልቶች እንደመሆናቸው መጠን እያንዳንዳቸው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው። እግዚአብሔር የጸጋ ስጦታን ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ መታነጽ ስለሰጠም እያንዳንዱ ም ዕመን በተሰጠው ስጦታ ጉባዔውን እንዲያንጽ ይጠበቅበታል።

ሁሉም ምዕመን በተጨማሪ የተቀደሰ ኑሮን በመኖር፣ወንጌልን ላልሰሙ በማሰማት፣እርስ በርስ በመተናነጽና በመገነባባት፣በታማኝነት በማምለክና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በመሳተፍ፣ በውዴታና በደስታ ለወንጌል አገልግሎት የሚውል የገንዘብ ስጦታን በመስጠት እግዚአብሔርን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን ሁለት የመገለጫ መልኮች ምን ምን ናቸው?

2. ሁሉ አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

3. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንስ?

4. አንድ አማኝ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆን ለምን ያስፈልገዋል?

5. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪ አገልጋዮች የትኞቹ ናቸው?

6. መሪዎች የተጠሩባቸው የተለያዩ ስሞች እነማን ናቸው?

7. እያንዳንዱ ምዕመን አገልጋይ ነው ወይስ አይደለም?

መ. የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶች

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ስርዓቶች ይካሄዳሉ። እነዚህ ሁለት ስርዓቶች የውሃ ጥምቀትና የጌታ ራት የሚባሉት ስርዓቶች ናቸው። ስርዓቶቹ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ስለሆነ ምዕመናን ደግሞ በስርዓቱ ተሳታፊ መሆን ይገባቸዋል።

1. የውሃ ጥምቀት

በብሉይ ኪዳን ህግ ሰው ወይም ዕቃ ቢረክስ በውሃ በመረጨት ወይም በመታጠብ ይነጻ ነበር (ዘኍ.19፡1-10፤ ዕብ.9፡9-10) የአዲስ ኪዳን የውሃ ጥምቀት ከብሉይ ኪዳን ህግ የተለየ ነው። የአዲስ ኪዳን የውሃ ጥምቀት ለመንጻት ሳይሆን ለመመሳሰል (ለመዋሃድ) የሚደረግ ስርዓት ነው።

በአዲስ ኪዳን የውኀ ጥምቀት ወይም ማጥመቅ የሚለው ቃል የተወሰደበት የግሪክ ቃል (baptizo) ባፕቲዞ የሚለው ሲሆን ትርጓሜው መድፈቅ፣ ውሃ ውስጥ መቅበር፣ ሙሉ በሙሉ ማጥለቅ ወይንም ማስጠም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊው የውኀ ጥምቀት ትርጉም መመሳሰል ማለት ነው። የውኀ ጥምቀት ጌታ ያዘዘው ትዕዛዝ ነው (ማቴ.16፡30-31)።

መጠመቅ ያለባቸው እነማን ናቸው? ብለን ብንጠይቅ እንደመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ ያመኑ ሁሉና ያመኑ ብቻ መጠመቅ አለባቸው (ሐዋ.2፡41፤ 8፡12፤ 36-38፤ 16፡14-15፤ 30-33፤ 18፡8፤ 19፡4-5)። የውኀ ጥምቀት ምሳሌያዊ የውህደት ወይም የአንድነት መግለጫ ድርጊት ነው፤ የሚያመለክተውም አማኝ ከክርስቶስ ጋር መመሳሰሉን ነው (ሮሜ.6፡1-10፤ ቆላ.2፡11-13)። አንድ አማኝ ክርስቶስን ባመነ ጊዜ የተለወጠውን የውስጥ ለውጥ በውጪያዊና በሚታይ መንገድ በአደባባይ በውኀ ጥምቀት ይመሰክራል።

የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ከክርስቲያን ጥምቀት የቀደመ የብሉይ ኪዳን ጥምቀት ነው። የዮሐንስ ጥምቀት ዋና ዓላማ ስለመሲህ ማለት ስለክርስቶስ በመስበክ ሰዎች ንስሃ ገብተው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁትና ሲመጣም እንዲቀበሉት ለማድረግ ነበር (ማቴ.3፡11-12፤ማር.1፡1-8፤ ሉቃ.3፡3-6)። ጌታማ ራሱ በ30 አመቱ በማየ ዮርዳኖስ (በዮርዳኖ ውኀ) በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል። ጌታችን የተጠመቀው ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ኃጢአቱን ለመናዘዝ ወይም ለመዘጋጀት ሳይሆን ጽድቅ ሁሉ ለመፈጸምና መሲሁ እርሱ መሆኑን ለመግለጥ ነበር (ዮሐ.1፡29-34)

ክርስቲያን በውኀ የሚጠመቀው ለደኅንነት አይለም። አንድ ክርስቲያን የሚድነው በ እምነት ጌታን በሚቀበልበት ጊዜ እንጂ ጥምቀትን ጨምሮ በሌላ በማናቸውም ስራ አይደለም። አንድ ክርስቲያን የሚጠመቅበት ምክንያት የጌታ

ት ዕዛዝ ስለሆነ እርሱን ለመታዘዝ እና የውስጡን ለውጥ በውጪያዊ መግለጫ ለመግለጥ ማለትም ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅ መነሳቱን ለማወጅ በዚህም ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ መሆኑን ለማሳወቅ ነው።

ማንም ክርስቲያን የወንጌሉን የምስራች ቃል ከሰማ በኋላ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን እንደ ግል መድኃኒቱ ከተቀበለ በኋላ የውስጡን ለውጥ በጥምቀት መመስከር እንደሚገባው ካወቀ መጠመቅ ይችላል። አንድ ክርስቲያን መጠመቅ ያለበት እንደ ጌታ ትዕዛዝ በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በኢየሱስ ስም የመጠመቅ ነገር ተዘግቧል። ይህ ማለት የመጀመሪያው አሳብ መሻሩ ሳይሆን በወቅቱ ኢየሱስን እንደ መሲህ ለመቀበል የነበረውን ችግር ለማስወገድ አትኩረትን በኢየሱስ ላይ ለማድረግ ነው እንጂ ትምህርተ ሥላሴን ውድቅ የማድረጋቸው እርምጃ ወይም “በአብ፣በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም” የተባሉትን መሻራቸው ወይም በዚያ ስም ያለማጥመቃቸው አልነበረም። ሰው አንድ ጊዜ ካመነ በኋላ መጠመቅ አለበት።

ጥያቄዎች

1. በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙት ሁለት ስርዓቶች ምንና ምን ናቸው? ______________________

2. የብሉይ ኪዳን የመርጨት ስርዓት ዓላማ ምን ነበር? ______________________

3. የአዲስ ኪዳን ማጥመቅ የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉም ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊውስ? ______________________

4. መጠመቅ ያለባቸው እነማን ናቸው? ______________________

5. የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ዓላማ ምን ነበር? ጌታስ ለምን በእርሱ ተጠመቀ? ______________________

6. አንድ ክርስቲያን የሚጠመቀው ለምንድነው? ____________________

____

7. ክርስቲያን መጠመቅ ያለበት መቼ ነው? ____________________

____

8. አንተስ ጌታን ከተቀበልክ በኋላ ተጠመቀሃል? ለመጠመቅስ ታስባለህ? የምታስብ ከሆነ የቤተ ክርስቲያንህን መሪዎች ማነጋገር ይኖርብሃል። ____________________

____

2. የጌታ ራት

ሌላው ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣት መጠበቅ ያለባት ስርዓት የጌታ ራት መታሰቢያ ወይም ቅዱስ ቁርባን የሚባለው ነው (ማቴ.26፡26-30፤ ማር.14፡22-26፤ ሉቃ.22፡17-20፤ 1ቆሮ.11፡23-34)። "ቁርባን" የሚለው የግዕዝ ቃል "መቅረብ" ከሚለው የዕብራይስጥ ስርወ-ቃል የወጣ ነው። በብሉይ ኪዳን በዘጸ.12 የዚህ ስርዓት ስር የሆነውን የፋሲካ በግ ታሪክ እናገኛለን። ጳውሎስ በ1ቆሮ.5፡7-8 ይህን ሲያወሳና ከዚህ ስርዓት ጋር ሲያያይዝው እናያለን። ይህን ስርዓት የደነገገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። የሰጠውም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት በሚበሉበት ጊዜ ነው። የፋሲካ በዓል ዋና ዓላማ እስራኤል ከግብጽ የመውጣታቸው መታሰቢያ ነው።

የጌታ ራት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሲል ስጋውን መቁረሱንና ደሙን ማፍሰሱን ደቀ መዛሙርቱን እንዲያስታውሱ የሰጣቸው ስርዓት ነው። በኢየሩሳሌም በነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህን ስርዓት በኅብረት ያደርጉ ነበር (ሐዋ.2፡42)። ከጌታ ጋር ራቱን ሲበሉ ጌታ እንደተናገራቸው እንጀራው የስጋው፤ ጽዋው ደግሞ የደሙ ምሳሌዎች ናቸው።

እነዚህ ነገሮች መታሰቢያ ብቻ ናቸውና የሚሰሩት ከህብስትና ከወይን ነው። የጌታ ራት ወይም ቅዱስ ቁርባን በሚወሰድበት መታሰብ የሚገባቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ጌታ ስለሰው ልጆች ሲል በመስቀል ላይ መሞቱን (1ቆሮ.11፡26) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደፊት ሊሆን ያለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽ ዓትን ነው (1ቆሮ.11፡2)።

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ስር ዓት የሚሳተፉት ሊመለከቱ የሚገባቸው ሌላ አቅጣጫም አለ፤ ይህም ወደ ራሳቸው (ወደ ውስጥ ህይወት) ነው (1ቆሮ.11፡28)። ይህም ማለት የጌታ ራት መታሰቢያ ከመካፈላቸው በፊት አማኞች ራሳቸውን መመርመር ማለትም ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ መሆኑን መመርመር ይገባቸዋል ማለት ነው። በሕይወታቸው ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ቢኖር መታሰቢያውን ከመውሰድ መቆጠብና ችግሮቻቸውን ቃሉ በሚለው መንገድ መፍታት ይኖርባቸዋል።

የጌታ ራት የኃጢአት ስርየት ማግኛ ወይም የደህንነት መንገድ አይደለም። ነገር ግን በጌታ ሞት ምክንያት መዳናችንን የምናስታውስበት፣ የጌታን መምጣት ተስፋ የምናስብበትና የምንናገርበት፤ አንድ እንጀራ በመቁረሳችንና አንድ ጽዋ በመጠጣታችን በአንድነታችን የምንደሰትበት ጊዜ ነው።

አማኞች ሁሉ የጌታን ራት የመካፈል መብት አላቸው። የሚካፈሉት ሁሉ ግን የተገባቸውና የገባቸው ሊሆኑ ያስፈልጋል (፲ቆሮ.፲፩፡27-32)። የተገባቸው ማለት ከላይ እንደተመለከትነው የዳኑና (ደህንነትን ያገኙ) በተጨማሪም በዚያ ጊዜ ከጌታም ሆነ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ የሆነ ማለት ነው። የገባቸው ማለት ደግሞ የጌታ ራት ምንነቱን የተረዱ ማለት ነው። ያለአግባብ የጌታን ራት መካፈል ድካምን፣ ህመምን፣ ስጋዊ ሞትን ፍርድንና ኩነኔንም ያስከትላል።

ክርስቲያኖች የጌታን ራት በሚካፈሉበት ጊዜ ብቃታቸው በጸጋው ብቻ መሆኑን በመገመትና በትህትና፤ ራስን በመመርመርና በመናዘዝ፤ የጌታን ሞትና የሰጠንን ደኅንነት በማሰብና በባለውለታነት፤ ዳግመኛ እንደሚመጣ በማሰብና በባለተስፋነት ከሞቱም የተነሳ ከሌሎች ጋር ስላለን ኅብረት በመደሰት፤ ለሌሎችም ሞቱን ለመናገር በመዘጋጀት መሆን ይገባዋል።

ጥያቄዎች

1. የጌታ ራት ስርዓት የተጀመረው መቼ ነው? ______________________________

2. የጌታ ራት ስርዓት መታሰቢያ ብቻ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ______________________________

3. የጌታ ራት ሲወሰድ መታሰብ የሚገባቸው ዋና ዋና ነገሮች ምን ምን ናቸው? ______________________________

4. የስርዓቱ ተሳታፊዎች የገባቸውና የተገባቸው መሆን አለባቸው ሲባል ምንድነው? ______________________________

5. ያለ አግባብ በቅዱስ ቁርባን መሳተፍ ምን ጉዳት አለው? ______________________________

6. ክርስቲያኖች ይህን ስር ዓት ለመፈጸም ማድረግ ያለባቸው ዝግጅት ምንድነው? ______________________________